ሰመጉ
HRCO

የሰብአዊ መብቶች ጉባዔ
HUMAN RIGHTS COUNCIL
ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው
HRCO stands for democracy, the rule of law *and* the respect of human rights

የምዝገባ ቁጥር
Reg. No. 1146

ታህሳስ 11 ቀን 2008 ዓ.ም

## <u>ጋዜጣዊ መግለጫ</u>

# ከአዲስ አበባና የኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላን ተቃውሞ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በአስቸኳይ ይቁሙ!

ከሕዳር 2008 መጨረሻ ጀምሮ የአዲስ አበባና ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከተሞችን የተቀናጀ የማስተር ፕላን በመቃወም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ከተሞች፣ በምዕራብ ወለጋ፣ በአርሲ፣ በባሌ እና በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ እንዲሁም በሌሎች የኦሮሚያ ዞኖች በሚገኙ በርካታ ከተሞች በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተቃውሞ ሰልፎች በመካሔድ ላይ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ የመንግስት ጸጥታ ሐይሎች ለተቃውሞ በወጡ ዜጎች ላይ በወሰዷቸው የኃይል እርምጃዎች እና በኂላም በጸጥታ ሐይሎችና ለተቃውሞ በወጡ ዜጎች መካከል በተነሱ ግጭቶችና ሰልፎቹን ተከትሎ በተፈጸሙ ድርጊቶች የበርካታ ዜጎች ህይወት አልፏል፣ ብዙዎች ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል፣ ዜጎች ታስረዋል፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ንብረትም ወድሟል፡፡ ሰመጉ ከተቃውሞው ጋር በተያያዘ በደረሰው ጉዳት የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ይገልጻል ፡፡

ዜጎች ሕይወታቸውና ኑሮዋቸውን በሚመለከቱ የመንግስት ዕቅዶች፣ ሕጎችና ፖሊሲዎች ላይ የመሳተፍ፣ የመወያየት፣ ሀሳብ የመስጠት፣ የመጠየቅና የመቃወም መብት እንዳላቸው በኢፌዲሪ ህገመንግስት ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ አሳታፊነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት የመልካም አስተዳደር እና የሰብዓዊ መብቶች መከበር መሠረቶች መሆናቸውም ይታወቃል፡፡ መንግስት የተቀናጀ የማስተር ፕላኑን በማርቀቅ ሂደት ዜጎችን፣ በተለይም በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ የኦሮሚያ ገጠር እና ከተማ ነዋሪዎችን ባለማሳተፉ፣ ረቂቅ ሰነዱንም እስከዛሬ ድረስ ለህዝብ ይፋ ባለማድረጉ፣ የብዙ ዜጎችን ሕይወት ለቀጠፈው እና የአካል እና የንብረት ጉዳት ላስከተለው ቀውስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ረቂቅ ማስተር ፕላኑ ለህዝብ፣ ለባለሙያዎች እና ለሌሎችም ባለድርሻ አካላት ቀርቦ ግልጽ ውይይት፣ ክርክር እና ትችት ሊደረግበት ሲገባ፣ ለዓመታት በምስጢር መያዙና ይዘቱም ለዜጎች አለመገለጹ፣ ለጥርጣሬ፣ ለውዥንብር እና ደም ላፋሰሰ ተቃውሞ መንስዔ ሆኗል፡፡

ማስተር ፕላኑ በህዝብ ላይ መፈናቀል ያስከትላል የሚል ጥርጣሬ እና ስጋት የገባቸው ዜጎች ተቃውሟቸውን ስርዓት ባለው መንገድ በሰላማዊ ሰልፍ የሚገልጹበት ሁኔታ በመንግስት አልተመቻቸም፡፡ በመሆኑም ከግቢያቸው ሳይወጡ ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን በገለጹና ተቃውሟቸውን ባሰሙ ተማሪዎች ላይ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች የወሰዱት አላስፈላጊ የኃይል እርምጃ ቀውሱ አሁን ለደረሰበት አስከፊ ደረጃ ጉልህ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ በዚህም የሁኔታዎች አያያዝ ጉድለት የተነሣ ተቃውሞአቸውን በሰላማዊ መንገድ ለመግለጽ ሰልፍ በወጡ ዜጎች እና በፀጥታ ሃይሎች መካከል አላስፈላጊ ውጥረት እና ግጭት ተከስቷል፡፡

የመንግሥት ያልተመጣጠነ የኃይል እርምጃ፣ ከመነሻው ሰላማዊ የነበረው ተቃውሞ ግብታዊ መልክ እንዲይዝና የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ እንዲባባስ በማድረግ ለዜጎች ሞት፣ አካል ጉዳት እና የህዝብ እና የግል ንብረት ውድመት ምክንያት ሆኗል። በግጭቱ ምክንያት መንገዶች በመዘጋታቸው፣ በአንዳንድ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ አካባቢዎች ተነስቶ የነበረውን የብሔር ግጭት በወቅቱ ለማብረድ እና ዜጎችን ከግድያ እና ንብረት መውደም ለመታደግ አስቸጋሪ አድርጎታል፣ ስለሆነም ለተጨማሪ የሰብዓዊ መብት ጥሰት አስተዋፅኦ አድርጓል።

በግጭቱ የፀጥታ ሀይሎች ከመጠን ያለፈ ኃይል በመጠቀማቸው በዜጎች ላይ ሞትና የአካል መጉደል ደርሷል የሚሉ አቤቱታዎችን ጨምሮ  ከተቃውሞው ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ሰመጉ በመመርመር ላይ ይገኛል። ሆኖም የተቃውሞው አድማስ በመስፋቱ እና በርካታ አካባቢዎችን ያካተተ በመሆኑ፣ ሰመጉ ባለው ውሱን አቅም ጉዳዩን ለማጣራት ተጨማሪ ጊዜ አስፈልጎታል። ምርመራው እንደተጠናቀቀም ሰመጉ ለህዝብ እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት የምርመራውን ውጤት ይፋ ያደርጋል። ሰመጉ የምርመራውን ውጤት ይፋ ከማድረጉ በፊት ይህንን ጋዜጣዊ መግለጫ ለማውጣት የተገደደው፣ በዜጎች ላይ እስካሁን ከደረሰው በላይ የከፋ ጉዳትና የሰብዓዊ መብት ጥሰት  እንዳይደርስ ሁሉንም ወገን ለማሳሰብ ነው።

በአሁኑ ወቅት ግጭቱ የመርገብ ሁኔታ የሚያሳይ እንኳን ቢሆን፣ መንግስት በተቃውሞው እንቅስቃሴ የተሳተፉ “ሽብርተኞች” ባላቸው ግለሰቦች ላይ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን አስታውቋል። ይህን ተከትሎም በርካታ ዜጎች በጸጥታ ሀይሎች በቁጥጥር ስር እየዋሉ እንደሆነ ሰመጉ ተገንዝቧል። በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የፍትህ ሥርዓቱና ፍርድ ቤቶች፣ በተለይ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ከሚታይባቸው የገለልተኛነትና የነጻነት ችግር አንጻር፣ የእነዚህ በጸጥታ ሀይሎች በቁጥጥር ስር የዋሉ ዜጎች ዕጣ ፈንታ ሰመጉን በእጅጉ ያሳስበዋል። በመሆኑም የእነዚህ ዜጎች አያያዝ፣ ምርመራ እና የፍርድ ሂደት ህገመንግስታዊ መብታቸውን ባከበረ መልኩ በፍጥነት እንከዲናወን፣ በምርመራ ወቅት በዜጎች ላይ የድብደባና የማሰቃየት ተግባራት እንዳይፈጸሙ መንግስት አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ሰመጉ አበክሮ ያሳስባል።

በተቃውሞ እንቅስቃሴው የተፈጸሙ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መንግስት በገለልተኛ አካል እንዲያጣራ፣ ለጥሰቱ ተጠያቂ የሆኑ አካላትን ለፍርድ እንዲያቀርብ፣ በግጭቱ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ተገቢው ካሳ እንዲከፈል እና ቤታቸው ለተቃጠለባቸው፣ ንብረት ለወደመባቸው እና ከኑሮዋቸው ለተፈናቀሉ ዜጎችም መልሶ የማቋቋም ስራ እንዲከናወን ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያ መንግሥት፣ ቀድሞም ሆነ ዛሬ ጥያቄና ችግር እንዲሁም የተለየ አጀንዳና አማራጭ አለን ከሚሉ ዜጎችና ስብስቦች ጋር ተቀምጦ የሚነጋገርበትና መግባባት የሚፈጠርበትን የውይይት ሥርዓት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲያደርግ ሰመጉ ይጠይቃል።

የፀጥታ ኃይሎች የዜጎችን ሰብዓዊ መብት እንዲያከብሩ፣ በተቃውሞ እንቅስቃሴው የሚሳተፉ ዜጎችም ተቃውሟቸውን ስርዓት ባለው፣ ሰላማዊ በሆነ እና ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ ብቻ እንዲገልጹ ሰመጉ ጥሪውን ያስተላልፋል። መላው ሕብረተሰብ፣ የሐይማኖት እና የፖለቲካ ተቋማት፣ መገናኛ ብዙኃን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ለዘመናት የኖሩት ተከባብሮ እና ተቻችሎ በሰላም የመኖር ዕሴቶች በዚህ ወቅት እንዳይሸረሸሩ እና የከፋ ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ሐገራዊ ቀውስ እንዳይፈጠር የየበኩላቸውንና የጋራም ጥረት እንዲያደርጉ ሰመጉ ያሳስባል።

**ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው**

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ /ሰመጉ/

አዲስ አበባ